<u>ስነ - ፅሁፍ</u>

- ❖ ስነ-ፅሁፍ - ዉበትና ለዛ ባለዉ ቋንቋ ተቀነባብሮ ገሀዱን አለም ፍንትዉ አድርጎ የሚያቀርብ የኪነ -ጥበብ ዘርፍ ነዉ።
- ❖ በቃል ሆነ በፅሁፍ ይቀርባል
- ❖ በሁለት አበይት ክፍሎች ይከፈላላል። እነሱም
    1. ቃላዊ ስነ- ፅሁፍ
    2. ፅሁፋዊ ስነ - ፅሁፍ

1. ቃላዊ ስነ -ፅሁፍ፡- ከትዉልድ ወደ ትዉልድ በቃል ይተላለፋል

- ከትዉልድ ወደ ትዉልድ በቅብብሎሽ ይተላለፋል

- ደራሲያቸዉ አይታወቅም

ቃላዊ ስነ - ፅሁፍ በዝርዉና በግጥም መልክ ይቀርባል።

በዝርዉ ከሚቀርቡ ቃላዊ ስነ- ፅሁፍ ዉስጥ

- ቀልድ
- እንቆቅልሽ
- ምሳሌያዊ አነጋገር
- ፈሊጣዊ አነጋገር
- አፈታሪክና ተረት

በግጥም የሚቀርቡ ቃላዊ ስነ- ፅሁፍ ዉስጥ

- ፋከራ
- ቀረርቶ
- የስራ ግጥሞች
- የልመና ግጥሞች
- የሀዘን ግጥሞች
- የሰርግ ግጥሞች

2 ፅሁፋዊ ስነ- ፅሁፍ፡- ደራሲያቸዉ የሚታዉቁና በፅሁፍ የሰፈሩ ናቸዉ። ፅሁፋዊ ስነ- ፅሁፍ ልበወለድ እና ኢ-ልበወለድ በመባል በሁለት ይከፈላሉ።

- ❖ ልብወለድ፡- ገሀዱን አለም መሰረት በማድረግ የሚቀርብ የፈጠራ ፅሁፍ ነዉ።
- ❖ ኢ-ልብወለድ - በተከናወኑ ወይም በድርጊት ላይ ተመስርቶ ዉብ በሆነ ቋንቋ የሚቀርብ ነዉ።

ልብወለድ በሁለት ሲከፈል ፡ እነሱም አጭር ልብወለድ እና ረጅም ልብወለድ ይባላሉ።

1. አጭር ልብወለድ፡- ከአስር ሺ ቃላት ባች የሚይዝ ተዉኔታዊነት የሚታይበት አጠር ያለ ትረካ ነዉ።
2. ረጅም ልብወለድ፡- የሰዉን የህይወት እንቅስቃሴ ከልደት እስከ ሞት ለማሳየት የሚሞክር ነዉ።

ኢ-ልብወለድ በታሪካዊ ና ሳይንሳዊ አቀራረብ ይቀርባል።

ስነ-ፅሁፍ

በግጥም

-የፋከራ
-የቀረርቶ
-የስራ
- የልመና
-የሰርግ፤
-የሀዘን

ልብጠለድ

ታሪካዊ

ሳይንሳዊ

ፅሁፋዊ ስነ-ፅሁፍ

ኢ-ልብጠለድ

አጭር ልብወለድ

ረጅም ልብወለድ

<u>መልመጃ አንድ</u>

<u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆኑ እዉነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ።</u>

________1. ፅሁፋዊ ስነ -ፅሁፍ ደራሲያቸዉ አይታወቅም

________2. ገሀዱን አለም መሰረት በማድረግ የሚቀርብ የፈጠራ ፅሁፍ ኢ-ልብወለድ ይባላል።

________3. ቃላዊ ስነ - ፅሁፍ በዝርዉና በግጥም መልክ መቅረብ ይችላል።

________4. ስነ - ፅሁፍ በፅሁፍ ማቅረብ አይቻልም

________5. ረጅም ልብወለድ የሰዉን ልጅ የህይወት እንቅስቃሴ ከልደት እስከሞት ያሳያል።